የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ‹√
አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24nd Year No.42
ADDIS ABABA 8th June, 2018

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፭/፪ሺ፲ ዓ.ም

የኢነርጂ (ማሻሻያ)አዋጅ
ቁጥር......................፲ሺ፫፻፷፫

**CONTENTS**

Proclamation No.1085 /2018

Energy (Amendment) Proclamation …………. 10363

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፭/ ፪ሺ፲

**የኢነርጂ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ**

የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ይህንኑ አዋጅ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፱ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩ .አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢነርጂ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፹፭/ ፪ሺ፲" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ማሻሻያ**

የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፱) ተተክቷል፤

"፱/'የኤሌክትሪክ ሥራ' ማለት የኤሌክትሪክ ዲዛይን፣ ኢንስታሌሽን፣ ጥገና፣ ፍተሻ፣

PROCLAMATION NO.1085/2018

**A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF ENEREGY PROCLAMATION**

**WHEREAS** , it has become necessary to amend the Energy Proclamation No. 810/2013;

**WHEREAS** ,the House of People Reperesentatives' of the Federal Democratic Republc of Ethiopia has ratified the said proclamation at its session held on the 17th day of May 2018;

**NOW THEREFOERE** , in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1 .Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Energy (Amendment) Proclamation No. 1085 /2018"

**2 .Amendment**

The Energy Proclamation No.810/2013 is hereby amended as follows:

1/ Sub-article (9) of Article 2 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new sub Article (9):

"9/' Electrical work' means work of electrical design, installation, maintenance, testing,

መቆጣጠር፣

ተቋራጭነት፣ ወይም ማማከር፣ የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራ ወይም ማንኛውም ሌላ የኤሌክትሪክ ነክ ሥራ ነው፤"

፪/ ከአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፭)፣ (፮) እና (⇔) ተጨምረዋል:-

"፭/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ባለፈቃድ ሥራ ያልጀመረው ከአቅም በላይ በሆነ አስገዳጅ ምክንያት መሆኑን ማመልከቻ አቅርቦ ባለስልጣኑም ይህንኑ ካረጋገጠ ፈቃዱን ለሁለት ጊዜ ብቻ በየዓመቱ ሊያድስ ይችላል፡፡

፮/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ባለፈቃድ ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ ሥራውን ሳይጀምር ከቀረ ወይም በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ወይም (ለ) የተደነገገውን ሁኔታ ያላከበረ እንደሆነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

⇔/ ባለፈቃዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት በፈቃዱ ላይ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመሩን ለባለስልጣኑ በሪፖርት ካሳወቀ እንደሁኔታው ባለሥልጣኑ ክትትል አድርጎ ማረጋገጡ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፈቃድ ዘመኑ ባለፈቃዱ ሥራ ስለመጀመሩ ሪፖርት ካደረገበት ጊዜ ጀምሮ የሚቆጠር ይሆናል፡፡"

፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ

inspection,

Contracting or consultancy, electro mechanical activity or any other electric related work;

2/ The following new sub articles (5) (6) and (7) are added after Sub article(4) of Article 8 of the proclamation;

"5/ Any licensee who has been issued license pursuant to sub-article (a) or (b) of Article 10 of this Proclamation if submits application to the Authority due to force majeure for his failure to commence the operation, the Authority, upon confirmation of causes, may renew the license only for two terms each for one year.

6/ Notwithstanding the provision of sub-article (5) of this Article, the license of any licensee shall, without any condition, be revoked if not commenced operation within two years or failed to comply with sub-article (a) and (b) of Article 10 of this Proclamation.

7/ When the licensee report to the Authority for the commencement of operation as specified in the license pursuant to sub-articles (a) and (b) of Article 10 of this Proclamation, as appropriate subject to the verification of the Authority, the license period shall start to count from the date of operation of the activity."

3/ Article (10 ) sub rticle 3 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (3), (a) (b) and (c) .

በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ)(ለ)(ሐ) በሚል ተተክቷል።

፲ሺ፫፻፷፭^

"ሀ/ ከጂኦተርማል ወይም ከውሃ ኃይል ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ሰው ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራ መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

ለ/ ከፀሐይ ኃይል፣ ከንፋስ፣ ከባዮማስ፣ ከድንጋይ ከሰል፣ ከተፈጥሮ ጋዝ ወ.ዘ.ተ. ኤሌክትሪክ ለማመንጨት ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ሰው ፈቃዱን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት ዓመት የጊዜ ገደብ ውስጥ ሥራውን መጀመርና ሥራውን ስለመጀመሩም ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ) ኤሌክትሪክ ኃይልን ከውጪ ማስመጣት ወይም ወደ ውጭ ሀገር መላክ ለመንግስት ብቻ የተከለለ ሥራ ነው።

## ፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፩ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**

a / Any person who obtained license for geothermal or hydropower to engage in the generation of electricity, shall commence electricity generation in accordance with the conditions of the licencese, the operation within five years from the date of 10365 :he license and accordingl[illegible] :he Authority about its commencement.

b / Any person who obtained license on solar, wind, biomass, coal, natural gas and others license to engage in the generation, electricity shall commence electricity generation ,in accordance with the conditions of the licence within three years of the issuance of a license, and accordingly report to the Authority about its commencement.

c/ Electricity export to or import is exlusively resereved for the government.

## 3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 8th day of June , 2018**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**